# ስለ ማመልከቻ ሂደት፣ የፕሮግራሞች ምርጫ፣ ኢመርሽን፣ እና የማግኔት ፕሮግራሞች መግቢያ ሂደት

# አማራጮች

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ

2025–2026



Montgomery County Public Schools
UNLEASHING POTENTIAL

## ዕሴት፡-

ትምህርት
መከባበር
መልካም ግንኙነት
ልህቀት/ምጡቅነት
ፍትኃዊነት

## ራእይ፡-

የወደፊት ዝግጁነት፡-
በተለዋዋጭ አለም ውስጥ ሁሉም ተማሪዎች ለእድገት፣ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ለመድረስ፣ እና ለስኬታማነት ዝግጁ ሆነው ይመረቃሉ—በማህበረሰባቸው ውስጥ እና ከዚያም በላይ ለመሪነት፣ ለአገልግሎት፣ እና በጎ ተጽእኖ ለመፍጠር በሚያስችላቸው እውቀት፣ ችሎታ፣ እና በራስ በመተማመን ተገንብተው ይመረቃሉ።

## ተልእኮ፡-

እምቅ አቅምን በተግባር እንዲገለጥ ማድረግ፥
ሁሉም ተማሪዎች ጥልቅ አስተሳሰብ ላይ የተመሰረተ፣ ትምህርትን የማዳበር እና የማበልጸግ እድሎችን በመጠቀም ጠንካራ የአካዳሚክ መሠረት ይኖራቸዋል።
ሁሉም ተማሪዎች ለውጦችን እና አዳዲስ ሁኔታዎችን መቋቋም የሚችሉ ሆነው ዕድሜ ልክ የመማር ፍላጎትና ጽናትን ያዳብራሉ።
ሁሉም ተማሪዎች ትርጉም ባለው ግንኙነት ላይ የተመሠረተ መስተጋብር፤ ውጤት ላይ የሚያተኩሩ እና በትብብር የሚሠሩ ይሆናሉ። ሁሉም ተማሪዎች በማህበረሰባቸው ውስጥ አዎንታዊ ተጽእኖ ለመፍጠር የተዘጋጁ፤ እና በግል ህይወታቸው እና በሙያዊ ብቃታቸው ለስኬታማነት የሚተጉ ይሆናሉ።


**የትምህርት ቦርድ**
Board of Education

**ሚ/ስ ጁሊ ያንግ** Ms. Julie Yang
**ፕሬዚደንት** President

**ሚ/ስ ግሬስ ሪቬራ-ኦቨን** Ms. Grace Rivera-Oven
**ም/ፕሬዚደንት** Vice President

**ሚ/ስ ሪታ ሞንቶያ** Ms. Rita Montoya

**ሚ/ስ ካርላ ሲልቨስትሪ** Ms. Karla Silvestre

**ወ/ሮ ላውራ ስቲዋርት** Mrs. Laura Stewart

**ሚ/ስ ብረንዳ ዎልፍ** Ms. Brenda Wolff

**ሚ/ስ ናታሊ ዚመርማን** Ms. Natalie Zimmerman

**ሚ/ስ አኑቫ ማሎ** Ms. Anuva Maloo
**ተማሪ አባል** Student Member

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ**
Montgomery County Public Schools

**ቶማስ W. ቴይለር (ዶ/ር)**
**የት/ቤቶች ሱፐር ኢንተንደንት**
Thomas W. Taylor, Ed.D., M.B.A.
Superintendent of Schools



15 West Gude Drive
Rockville, Maryland 20850
www.montgomeryschoolsmd.org

# ማውጫ


- መግለጫ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3
- MCPS የአውቶቡስ ማጓጓዣ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .


## የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮግራሞች


የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ማመልከቻ ፕሮግራም ቦታዎች/ማፕ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . 5

- የአካባቢ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮግራሞች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 6
- በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት የሚሰጥ የዓለም ቋንቋዎች ኢመርሽን ፕሮግራሞች . . . . . . . . . 7
- የአንደኛ ደረጃ የዳበረ ትምህርት ማዕከል . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 8


## የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮግራሞች


የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ማመልከቻ ፕሮግራም ቦታዎች/ማፕ. . . . . . . . . . . . . . . . . 10

- የአካባቢ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮግራሞች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 11
- የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት አለም አቀፍ ቋንቋዎች ኢመርሽን ቀጣይ ፕሮግራሞች . . . . . 12
- ሒሳብ፣ ሳይንስ፣ ኮምፒውተር ሳይንስ ማግኔት ፕሮግራም. . . . . . . . . . . . . . . . 13
  ሮቤርቶ W. ክሌሜንቴ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት እና ታኮማ ፓርክ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት
- ሰብአዊነት እና ኮሚዩኒኬሽን የማግኔት ፕሮግራም. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 14
  ዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁ/ር መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና
  ኢስተርን መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
- ዲጅታል ዲዛይን እና ደቨሎፕመንት ማግኔት ትምህርት ቤት . . . . . . . . . . . . . . 15
  አርግየል መካለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
- የፈጠራ እና ክዋኔ ስነጥበብ ማግኔት ትምህርት ቤት. . . . . . . . . . . . . . . . . . . 16
  ኤ. ማሪዮ ሎይደርማን መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
- ኤሮስፔስ ቴክኖሎጂ ማግኔት ትምህርት ቤት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 17
  ፓርክላንድ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት


## የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፕሮግራሞች - 9ኛ ክፍል


የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መስፈርቶችን ለሚያሟሉ የማመልከቻ ፕሮግራም ቦታዎች/ማፕ. . . . 19

ሪጅናል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ዕጣ (ሎተሪ) መሰረት ያደረገ የማመልከቻ ቦታዎች/ማፕ. . . . 20

- MCPS የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሪጅናል/ካውንቲ አቀፍ
  ፕሮግራሞች ማመልከቻ በጨረፍታ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 21
- የአካባቢ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፕሮግራሞች . . . . . . . . . . . . . . . . . . 22
- በኖርዝኢስት ኮንሰርቲየም ለሚኖሩ ተማሪዎች አማራጭ ፕሮግራሞች . . . . . . . . . . 23
- ዳወንካውንቲ ኮንሰርቲየም ለሚኖሩ ተማሪዎች አማራጭ ፕሮግራሞች . . . . . . . . . . 24


## ሙያ እና ኮሌጅ – ከ10ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ተማሪዎች


ካውንቲ አቀፍ ኮሌጅ እና ስራ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ቦታዎች/ካርታ . . . . . . . 26

- MCPS ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሪጅናል/ካውንቲ አቀፍ
  የሚያመለክቱበት ፕሮግራሞች በጨረፍታ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 27

## ◈ መግለጫ

በዚህ መጽሔት ላይ የሚገኘው መረጃ  የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አንደኛ ደረጃ፣ መካከለኛ ደረጃ፣ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያላቸውን የተለያዩ ፕሮግራሞች እንዲያውቁ ተማሪዎችን እና ቤተሰቦችን ለመርዳት የተዘጋጀ ነው። እያንዳንዱ ፕሮግራም በተማሪ ፍላጎትና ዝንባሌ ላይ የተመሰረተ የበለፀገ የመማር እድል እንዲሰጥ የታለመ ነው። ስለተማሪ የትምህርት አማራጮች በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት ይህንን መጽሔት እንደ ማጣቀሻ መጠቀም ይቻላል። ነገር ግን፣ በካውንቲው ስለሚገኙት እያንዳንዱ ልዩ ፕሮግራም ይህ መጽሔት አይገልጽም።

በዚህ መጽሔት ላይ ከተገለጹት ፕሮግራሞች በተጨማሪ፣ ትምህርት ቤቶች በየግላቸው በአካባቢ ክልል ነዋሪ ለሆኑ ተማሪዎች ብቻ ልዩ ፕሮግራሞችን ለመስጠት ይችላሉ።

## አማራጮችን መቃኘት

### ይህን ቡክሌት ከማንበብዎ በፊት እራስዎን ለሚጠይቁ ጥያቄዎች ይዘጋጁ

- ለእኔተማሪ ምርጡ የትምህርት አካባቢ ምንድነው?
- የእኔ ተማሪ ፍላጎቶች እና ትምህርታዊ ዝንባሌዎች ምንድናቸው?
- የአካባቢያችን ትምህርት ቤት የፕሮግራም ዝግጅት የእኔን ተማሪ ፍላጎቶች እና ዝንባሌዎች እንዴት ያሟላል?
- አስፈላጊ ከሆነ ለተማሪዬ ወደ አማካይ የአውቶቡስ ማቆሚያ መጓጓዣ ማዘጋጀት እችላለሁ?

### ይህንን መጽሔት ሲያነቡ...ይዘጋጁ

- ከፕሮግራሞቹ መካከል ለተማሪዬ ፍላጎቶች እና ዝንባሌዎች ተዛማጅነት የሚኖራቸው አሉ?
- ከአካባቢያችን ውጪ ወደ ትምህርት ቤት መጓዝ በቤተሰባችን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችለው እንዴት ነው?
- ለዚህ ፕሮግራም መጓጓዣ ይቀርባል?

**GO!  ይቀጥሉ!**

### ይህንን መጽሔት ካነበቡ በኋላ ..

- በአካባቢያችን ትምህርት ቤት ለተማሪዬ ያሉትን አማራጮች በተገቢ ሁኔታ ተመልክቻለሁ?
- ፕሮግራሙ ለተማሪዬ ፍላጎቶች እና ዝንባሌዎች ጥሩ ተዛማጅነት አለው?
- ጥያቄዎችን ለመጠየቅ እና የማመልከቻ ቅጾችን ማንን ማግኘት እንዳለብኝ አውቃለሁ?
- የማመልከቻውን ወይም የምርጫ ሂደቱን ከመጀመሬ በፊት ከተማሪዬ ጋር ስለተለያዩ አማራጮች ተወያይቻለሁ?
- ስለ ማጓጓዣ ዝግጅት እና የመጠባበቂያ እቅድ በጥንቃቄ አስቤበታለሁ?

## ◈ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የአውቶቡስ መጓጓዣ

MCPS ደንብ EEA-RA የተማሪ መጓጓዣ፣ ሰክሽን II.B.2፣ “የአውቶቡስ አገልግሎት ማእከል፣ ከሰፈር የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ማዕከላዊ ቦታ ወደ ፕሮግራሙ ቦታ መጓጓዣ ተብሎ የተገለጸው ሊሆን ይችላል፥ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አማራጭ የካውንቲ አቀፍ ፕሮግራሞች መመሪያ መጽሔት ውስጥ በተገለጹት ልዩ ፕሮግራሞች ላይ ለሚማሩ ተማሪዎች በቦርድ የተግባር ድንጋጌ፣ የሚማሩባቸው ቦታዎች፣ የትራንስፖርት አገልግሎቶች እና የባጀት ምደባ ደረጃዎች ተሰጥተዋል። ወላጆች/አሳዳጊዎች ተገቢ የእግረኛ መንገድ ቢኖርም ባይኖርም ከአማካይ የአውቶብስ ማቆሚያዎች ለተማሪዎች መጓጓዣ የማቅረብ ሃላፊነት አለባቸው። ማዕከላዊ ማቆሚያዎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤቶች እና በሌሎች የመንግስት መገልገያዎች ይመደባሉ። ሁሉ ተማሪዎች ከቤታቸው በእግር ጉዞ ርቀት ላይ የአውቶቡስ ማቆሚያ ላይኖራቸው ይችላል። የመጓጓዣ አማራጮች እና ኃላፊነትን በሚመለከት በጥንቃቄ ማገናዘብ አስፈላጊ ነዉ።




በዚህ መጽሔት ውስጥ (በስተግራ) የአውቶቡስ ምስል ይመለከታሉ፡- እባክዎ ስለ እያንዳንዱ ፕሮግራም መጓጓዣ ለማወቅ ከምስሉ ቀጥሎ ያለውን መረጃ ያንብቡ። ምንም ምስል ከሌለ፣ ለዚያ ፕሮግራም የተለየ የመጓጓዣ አማራጭ የለም ማለት ነው። ስለዚህ "የመደበኛ ትምህርት የመጓጓዣ ደንቦች" ተግባራዊ ይሆናሉ።

ስለ ትራንስፖርት ደንቦች ለበለጠ መረጃ፣እባክዎ የትራንስፖርት ድረ ገጽ www2.montgomeryschoolsmd.org/departments/transportation/ ይጎብኙ ወይም 240-740-6200 ይደውሉ።

## በአካባቢ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮግራሞች

## የአለም አቀፍ ቋንቋዎች ኢመርሽን ፕሮግራሞች
(ቋንቋውን አዘውትሮ በመጠቀም የውጭ ቋንቋን የማስተማር ዘዴ፣ አብዛኛውን ጊዜ በልዩ ትምህርት ቤት የሚሰጥ ነው)

## አንደኛ ደረጃ የበለፀገ ጥናት ማዕከል

የወላጆች/አሳዳጊዎች እና ተማሪዎች ትኩረት፡ ከዚህ ሕትመት በኋላ አንዳንድ መረጃ ሊለወጥ ይችላል። እባክዎ ይህን ድረገጽ ይጎብኙ፡-www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/specialprograms/ ወይም ስላሉት ፕሮግራሞች ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት ትምህርት ቤቱን ያነጋግሩ።




***World Languages Immersion, Grades K-5***
*For more information - 240-740-4005*

*In **partial immersion** programs, approximately one half of the day is spent learning subjects such as science and math in the immersion language.*

*In **fulll immersion** programs, all of the core subjects are taught in the immersion language. The world language is not taught explicitly, but used as the language of instruction so that students learn the language while learning the content of the curriculum.*

***Chinese Immersion***

***Potomac Elementary School (partial immersion)***
*Continued at Herbert Hoover Middle School Local program*

***Bayard Rustin Elementary School (partial immersion)***
*Continued at Herbert Hoover Middle School Countywide program*

***French Immersion***

***Maryvale Elementary School (full immersion)***
*Continued at Gaithersburg Middle School*
*Available to students living in the following high school clusters:*
*Blake, Churchill, Damascus, Gaithersburg, Magruder, Richard Montgomery, Northwest, Paint Branch, Poolesville, Quince Orchard, Rockville, Seneca Valley, Sherwood, Springbrook, Watkins Mill, Wheaton, Wootton*

***Sligo Creek Elementary School (full immersion)***
*Continued at Silver Spring International Middle School*
*Available to students living in the following high school clusters:*
*Blair, Blake, Bethesda Chevy-Chase, Einstein, Walter Johnson, Kennedy, Northwood, Paint Branch, Springbrook, Whitman*

***Spanish Immersion***

***Burnt Mills Elementary School (full immersion)***
*Continued at White Oak Middle School*

***William Tyler Page Elementary School (full immersion)***
*Continued at White Oak Middle School*

***Rock Creek Forest Elementary School (full immersion)***
*Continued at Westland Middle School*
*Countywide program*

***Center for Enriched Studies*, Grades 4-5***
*For more information - 240-740-3110*

*Each center draws from a specific geographic region, generally aligned to high school clusters with some exceptions. A student's home address determines the CES location for which they are eligible. CES centers are currently located at the following elementary schools:*

***Lucy Barnsley Elementary School***
*Richard Montgomery, Rockville, and Wheaton high school clusters.*
***Chevy Chase Elementary School***
*Bethesda-Chevy Chase, Walter Johnson, and Whitman high school clusters.*
***Clearspring Elementary School***
*Clarksburg and Damascus high school clusters.*
***Cold Spring Elementary School***
*Churchill and Wootton high school clusters.*
***Dr. Charles R. Drew Elementary School***
*Blake, Paint Branch, Sherwood, and Springbrook high school clusters.*
***Fox Chapel Elementary School***
*Northwest, Poolesville, Quince Orchard, and Seneca Valley high school clusters.*
***Mill Creek Towne Elementary School***
*Magruder, Gaithersburg, and Watkins Mill high school clusters.*
***Pine Crest Elementary School/Oak View Elementary School***
*Blair, Einstein, Kennedy, and Northwood high school clusters.*

*Piney Branch, Stonegate, Rachel Carson, and Spark Matsunaga Elementary schools have local CES programs.*

*Montgomery County Public Schools - Division of Capital Planning - August 26, 2025*

# የአካባቢ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮግራሞች

### የተፋጠነ እና የበለጸገ ትምህርት ክፍል/ Division of Accelerated and Enriched Instruction

240-740-3110
www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/enriched/

### የሒሳብ ትምህርት

240-740-4001
www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/math/

### የቋንቋ ስነጥበብ ትምህርት

240-740-4006
www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/english/

### የሳይንስ ትምህርት

240-740-4002
www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/science/

### የማህበራዊ ጥናት ትምህርት

240-740-4008
www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/socialstudies/

ሁሉም የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች የተማሪዎችን ፍላጎት ለማሟላት የሚያስችሉ የማስተማርያና የዳበሩ ፕሮግራሞች አሏቸው፣ ከፍተኛ ፍላጎትና ዝንባሌ ለሚያሳዩ ጭምር ልዩ የጥናት ዘርፍም ያካትታል። በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ፣ ሁሉም ተማሪዎች ትምህርታቸዉን የማጎልበት እና የማስፋት፣በሚፈልጉት መስክ የማጥናት እና የመመራመር፣ እና ፈታኝ እና ጥብቅ ጥናቶችን ከእኩዮቻቸው ጋር ተባብረው እንዲሠሩ እድል ሊኖራቸው ይገባል።

### የእርስዎን አካባቢ ትምህርት ቤት ያነጋግሩ

የአከባቢዎ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስለሚያቀርበው ትምህርት የበለጠ ለማወቅ ት/ቤቱን በቀጥታ ያነጋግሩ እና/ወይም የትምህርት ቤቱን ድረ ገጽ MCPS መነሻ ገጽ ላይ ይጎብኙ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/schools/ እያንዳንዱ ት/ቤት የተማሪዎቹን ፍላጎቶች ለማሟላት የተለያዩ የትምህርት ፕሮግራሞች ሞዴሎችን ይጠቀማል።

### በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ፣ ሁሉም ተማሪዎች ለ..እድል አላቸው፡-

- የክፍል ደረጃቸውን ማቴሪያሎች በጥልቀት የመረዳት እና የማዳበር
- ከክፍል ደረጃቸውም በላይ የሆኑ ማቴሪያሎችን በጥልቀት የማወቅና የማዳበር
- የዝንባሌዎቻቸውን አቅጣጫ ለማወቅ ማጥናት እና ማሰስ
- አዳጋች እና ጠጣር ሥራዎችን ከእኩዮቻቸው ጋር በመተባበር መሥራት

### ተማሪ ፍላጎት፣ ዝንባሌ፣ ወይም በአንድ ጥናት ዙርያ ጥሩ ክንውን በሚያሳይበት/በምታሳይበት ጊዜ፣ በሁሉም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይህን የፍላጎት ደረጃ ለማሟላት የሚያስችሉ ልዩ ልዩ ዓይነት የማስተማር እና የማዳበር ፕሮግራሞች ይኖራቸዋል። አንዳንድ ሊሆኑ የሚችሉ ምሳሌዎች...

- ከፍተኛ የትምህርት ችሎታ ላላቸው ተማሪዎች ዊልያም እና ሜሪ የቋንቋ ስነጥበብ ዩኒት ከ 2ኛ-5ኛ ክፍል
- ጁንየር ግሬት ቡክስ ፕሮግራም K–5ኛ ክፍሎች
- የዳበረ እና ዳጎስ ያለ የሂሳብ ስራ ተደራሽነት
- የዳበረ ሊተርሲ
- የሳይንስ አውደ ርእይ
- ጂኦግራፊ ንብ (Geography Bee)
- ት/ቤት አቀፍ የማበልጸግ ፕሮግራም
- ኢንተርናሽናል ባከሎሬት የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ፕሮግራም
- የስነጥበብ ቅይጥ ሞዴል

# የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዓለም አቀፍ ቋንቋ ኢመርሽን ፕሮግራሞች

## ለምዝገባ አስፈላጊ ነገሮች

**በርንት ሚልስ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ስፓንሽኛ)**
በርንት ሚልስ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎችን፣ እንዲሁም ከሌሎች አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወደ ፍራንሲስ ስኮት ኪይ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገቡ ተማሪዎችን ያገለግላል። ቦታ ከተገኘ፣ ለሌሎች ተማሪዎችም ክፍት ይሆናል።

**ባያርድ ረስቲን አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት** (ቻይንኛ/Chinese—በከፊል/Partial)
ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክለስተሮች ሁሉንም ተማሪዎች ያገለገግላል።

**ሜሪቬሌ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት** (ፈረንሳይኛ)
ከሚከተሉት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክለስተሮች ተማሪዎችን ያገለግላል:-

ብሌክ*፣ ቸርችል፣ ደማስከስ፣ ጌትስበርግ፣ ማግሩደር፣ ሪቻርድ ሞንትጎመሪ፣ ኖርዝዌስት፣ ፔይንት ብራንች*፣ ፑልስቪል፣ ኩዊንስ ኦርቻርድ፣ ሮክቪል፣ ሴኔካ ቫሊ፣ ሸርውድ፣ ስፕሪንግብሩክ*፣ ዋትኪንስሚል፣ ዊተን፣ እና ውተን።

**ዊሊያም ቲ. ፔጅ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት** (ስፓንሽኛ)
ዊሊይም ቲ. ፔጅ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎችን ያገለግላል። ቦታ ከተገኘ ከሌላ ክለስተሮች ለሚመጡ ተማሪዎችም ክፍት ይሆናል።

**ፖቶማክ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት** (ቻይንኛ/Chinese—በከፊል/Partial)
ፖቶማክ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚከታተሉ ተማሪዎችን ያገለግላል። ቦታ ከተገኘ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክለስተር ተማሪዎች ሁሉ ክፍት ይሆናል።

**ሮክ ክሪክ ፎረስት አንደኛ ደረጃ ት/ቤት** (ስፓንሽኛ)
ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክለስተሮች ሁሉንም ተማሪዎች ያገለገግላል።

**ስላይጎ ክሪክ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት** (ፈረንሳይኛ)
ከሚከተሉት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክለስተሮች ተማሪዎችን ያገለግላል:- ብሌየር፣ ብሌክ*፣ ቤተስዳ-ቼቪ ቼዝ፣ አልበርት አንስታይን፣ ዋልተር ጆንሰን፣ ኬኔዲ፣ ኖርዝውድ፣ ፔይንት ብራንች*፣ ስፕሪንግብሩክ* እና ዋልት ዊትማን።

*ብሌክ፣ ፔይንት ብራንች ወይም ስፕሪንግብሩክ አካባቢዎች የሚኖሩ ተማሪዎች እንደመኖሪያ አድራሻቸው በሜሪቬሌ ወይም ስላይጎ ክሪክ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት የፈረንሳይኛ ኢመርሽን ፕሮግራም ይከታተላሉ። ለተጨማሪ መረጃ ይህን ድረገጽ ይጎብኙ:- https://docs.google.com/document/d/149SZ6uv91yE957PvFXQYhJ4cO4zZbMAVVuctLZmAKDU/preview

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዓለም ቋንቋዎች ኢመርሽን ፕሮግራሞች (በሚማሩበት የውጭ ቋንቋ አዘውትሮ በመጠቀም የውጭ ቋንቋን የማስተማር ዘዴ፣ አብዛኛውን ጊዜ በልዩ ትምህርት ቤት የሚሰጥ የቋንቋ ትምህርት ነው) በመዋዕለ ህጻናት የሚጀምር ሲሆን እስከ 5ኛ ክፍል ይቀጥላል። የኢመርሽን ፕሮግራሞች በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት 6ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ድረስ ይቀጥላሉ። በእነዚህ ፕሮግራሞች ተማሪዎች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ከሪኩለምን ከሦስት በአንዱ ቋንቋ ይማራሉ።—ቻይንኛ/Chinese፣ ፈረንሳይኛ/French፣ ወይም ስፓንሽ/Spanish።

MCPS በአሁኑ ጊዜ ባለሁለት መንገድ ኢመርሽን ፕሮግራሞችን (ስፓኒሽ-እንግሊዘኛ) በስድስት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (ብራውን ጣቢያ፣ ጋይዘር በርግ፣ ኬምፕ ሚል፣ ኦክላንድ ቴራስ፣ ሮሊንግ ቴራስ እና ዋሽንግተን ግሮቭ) ያቀርባል። የተናጠል ትምህርት ቤቶች ሞዴሎች በጊዜ ሠንጠረዥ ቢለያዩም፣ ሁሉም ፕሮግራሞች 50/50 ሞዴል ይከተላሉ፣ ይህም 50% ትምህርት በእያንዳንዱ የፕሮግራም ቋንቋ ይሰጣል ማለት ነው። የሁለት አቅጣጫ ኢመርሽን ፕሮግራሞች ክፍት የሆኑት በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ለተመዘገቡ ተማሪዎች ብቻ ነው።

### ወደ ፕሮግራሙ ለመግባት

ወደ MCPS አንደኛ ደረጃ ት/ቤት አለም አቀፍ ቋንቋዎች ኢመርሽን ፕሮግራም መግቢያ ውስን ነው። ለሙዓለ ህፃናት እና ለ1ኛ ክፍል ተማሪዎች ምርጫ የሚደረገው በሎተሪ/በእጣ ሲስተም ነው። የዚህ ዓይነት ዕጣ/ሎተሪ ከዚህ በታች ያሉትን እውነታዎች ግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ሊሆን ይችላል:- (a) በመድብለ ቋንቋ ትምህርት ፕሮግራም ላይ ያለ(ች) ታላቅ ወንድም/እህት ሌላ ታናሽ ወንድም/እህት ለመግባት በሚፈልግበት-በምትፈልግበት ዓመት በመድብለ ቋንቋ ትምህርት ፕሮግራም ለመቀጠል የሚፈልግ/የምትፈልግ ከሆነ፥ (b) የማህበራዊ-ኤኮኖሚያዊ አቋምና ድህነት፣ እና (c) ሌሎችም በሱፐርኢንተንደንት አማካይነት ተለይተው የሚቀርቡ፥ አካባቢው የሚሸፍናቸው እንደ ልዩ ሁኔታ የሚታዩ ምክንያቶች። 2017-2018 የትምህርት አመት በቋንቋ ኢመርሽን ፕሮግራም የተመዘገበ(ች) ታላቅ ወንድም ወይም እህት ያለው/ያላት እና በዚህ ፕሮግራም የሚቀጥል/የምትቀጥል ማንኛውም ተማሪ በተመሳሳይ የቋንቋ ትምህርት ፕሮግራም ታናሽ ወንድም ወይም እህት ለመመዝገብ በሚፈልግበት/በምትፈልግበት የትምህርት አመት፣ ወደፕሮግራሙ ለመግባት ዕጣ/ሎተሪ ሳያስፈልግ በቋንቋ ኢመርሽን ፕሮግራም መመዝገብ ይችላል/ትችላለች። ሆኖም ስለተማሪው(ዋ) የኢመርሽን ፍላጎት ቅጽ ተሞልቶ መቅረብ አለበት። አዲስ ተማሪዎች የሚገቡት 1ኛ ክፍል ካጠናቀቁ በኋላ ቦታ ከተገኘ እና ተማሪዎች የመግቢያ ፈተና ካለፉ ነው። በኢመርሽን ፕሮግራሙ ላይ መሳተፍ ለሚፈልግ ለእያንዳንዱተማሪ ወላጆች/አሳዳጊዎች የፍላጎት መግለጫ ቅጽ ሞልተው ማቅረብ አለባቸው። ስለ ሂደቱ የበለጠ መረጃ ለማግኘት:- www2.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/specialprograms/admissions/immersion ይጎብኙ፣ ወይም 240-740-7800 ይደውሉ።

### የእርስዎ ተማሪ ...ይፈልጋሉ?

- በፈረንሳይኛ መጽሐፍ እንዲያነብ/እንድታነብ
- ስለ ወቅታዊ ጉዳዮች በስፓንሽ ቋንቋ ውይይት እንዲያደርግ/እንድታደርግ?
- የሒሳብ ፕሮብሌሞችን/ስሌቶችን በቻይንኛ እንዲሠራ-እንድትሠራ?
- የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ካሪኩለም እየተከተለ(ች)ም ሁለተኛ ቋንቋ እንዲማር/እንድትማር?

### ከዓለም ቋንቋዎች ኢመርሽን ፕሮግራሞች ውስጥ ለአንዱ ማመልከት ያስቡ።(በሚማሩበት ቋንቋ አዘውትረው በመጠቀም የውጭ ቋንቋን የማስተማር ዘዴ ሲሆን፣ አብዛኛውን ጊዜ በልዩ ትምህርት ቤቶች የሚሰጥ ትምህርት ነው)።

የቋንቋ ኢመርሽን ማለት ተማሪዎች የከሪኩለምን ይዘት በሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩበት ትምህርታዊ ስልት ነው።(አብዛኛውን ጊዜ በሚማሩበት ቋንቋ አዘውትረው በመጠቀም የውጭ ቋንቋን የማስተማር ዘዴ ሲሆን፣ በልዩ ትምህርት ቤቶች የሚሰጥ ትምህርት ነው)።

በዚህ ዓይነት፣ የኢመርሽን ተማሪዎች ይዘቱን መማር ብቻ ሳይሆን፣ በትምህርቱ ውስጥ የቋንቋውንም እውቀት ያገኛሉ። ሙሉ-ኢመርሽን ፕሮግራሞች ውስጥ፣ ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ ዋና ትምህርቶቻቸውን (ማንበብ፣ መጻፍ፣ ሂሳብ፣ ማህበራዊ ጥናቶች እና ሳይንስ) ይማራሉ። ከፊል-ኢመርሽን ፕሮግራም በተመሣሣይ መርህ የተመሠረተ ሲሆን በከፊል ከሪኩለሙ በሁለተኛ ቋንቋ ይሰጣል። በኢመርሽን መቼት እና ዓለም አቀፍ ቋንቋዎች ትምህርት መካከል ዋናው ልዩነት የሁለተኛ ቋንቋ መማር-ማስተማር አቀራረብ ነው። በኢመርሽን ፕሮግራም፥ ቋንቋ ትምህርቱን ሳይሆን ይዘቱን ማስተማሪያ ስልት ነው።(አብዛኛውን ጊዜ በሚማሩበት ቋንቋ አዘውትረው በመጠቀም የውጭ ቋንቋን የማስተማር ዘዴ ሲሆን፣ በልዩ ትምህርት ቤቶች የሚሰጥ የውጭ ቋንቋ ትምህርት ነው)።

የእያንዳንዱን ትምህርት ቤት ድረ ገጽ ለመጎብኘት፣ የትምህርት ቤቱን ስም MCPS በይነመረብ ላይ ይፈልጉ ወይም www.montgomeryschoolsmd.org/schools/ ይጎብኙ።

### አለም አቀፍ ቋንቋዎች ትምህርት 240-740-4005

www2.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/specialprograms/admissions/immersion




የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለአንዳንድ አካባቢ በርካታ የኤለመንተሪ ት/ቤት ቋንቋ-ኢመርሽን ፕግሮግራሞች ከአማካይ ሥፍራ ማቆሚያዎች የመጓጓዣ አገልግሎት ይሰጣል። የትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦትን በተመለከተ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት በአስተናጋጁ ትምህርት ቤት የፕሮግራሙን አስተባባሪ ያነጋግሩ። ስለ ማጓጓዣ "አማካይ የማቆሚያ ቦታዎች" የበለጠ መረጃ ለማግኘት እባክዎ ገጽ 3 ይመልከቱ።

## አንደኛ ደረጃ የዳበረ ትምህርት ማዕከል

የዳበረ የኤለመንተሪ ጥናት ማዕከል ለ 4ኛ እና 5ኛ ክፍል ተማሪዎች ነው። በጂኦግራፊ ክልሎች የተዘጋጀ መርሃ ግብር በሚከተሉት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ይገኛል፡-

### ሉሲ ቪ. ባርንስለይ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
ሪቻርድ ሞንትጎመሪ፣ ሮክቪል እና ዊተን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክለስተር።

### ቼቪ ቼዝ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት
ቤተዝዳ ቼቪ ቼዝ፣ ዋልተር ጆንሰን፣ እና ዋልት ዊትማን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክለስተሮች።

### ክሊርስፕሪንግ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት
ክላርክስበርግ *፣ ደማስከስ እና ሴኔካ ቫሊ * ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ክለስተር።
*ክላርክስበርግ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት፣ ዊምስ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት፣ ጊብስ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት እና ካቢን ብራንች አንደኛ ደረጃ ት/ቤት

### ኮልድ ስፕሪንግ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት
ቸርችል እና ውተን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክለስተሮች።

### ዶ/ር ቻርልስ ር. ድሪው አንደኛ ደረጃ ት/ቤት
ብሌክ (Blake)፣ ፔይንት ብራንች (Paint Branch)፣ ሼርውድ (Sherwood)፣ እና ስፕሪንግብሩክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Springbrook high school) ከለስተሮች።

### ፎክስ ቻፕል አንደኛ ደረጃ ት/ቤት
ክላርክስበርግ*፣ ኖርዝዌስት፣ ፑልስቪል፣ ኩዊንስ ኦርቻርድ፣ እና ሴኔካ ቫሊ* የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ክለስተር።
*ክሎፐር ሚል አንደኛ ደረጃ ት/ቤት፣ ጀርመንታወን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት፣ መከሉፍ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት፣ ራይድ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት፣ ሌክ ሴኔካ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት፣ ዋተርስ ላንዲንግ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት፣ ዳሊ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት፣ እና ፎክስ ቻፕል አንደኛ ደረጃ ት/ቤት

### ሚል ክሪክ ታወነ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት
ጌትስበርግ፣ ኮሎ. ዛዶክ ማግሩደር፣ እና ዋትኪንስ ሚል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ክለስተሮች።

### ኦክ ቪው አንደኛ ደረጃ ት/ቤት
ብሌር፣ አልበርት አንስታይን፣ ኬኔዲ እና ኖርዝዉድ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክለስተሮች በተለይ ኢስት ሲልቨር ስፕሪንግ፣ ፍሎራ ሲንገር፣ ፎረስት ኖልስ፣ ሃይላንድ ቪው፣ ኦክ ቪው፣ ሮሊንግ ቴረስ፣ ስላይጎ ክሪክ፣ ውድሊን አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች.

### ፓይን ክረስት አንደኛ ደረጃ ት/ቤት
ብሌየር፣ አልበርት አንስታይን፣ ኬኔዲ፣ እና ኖርዝዉድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ክለስተር በተለይ አርኮላ፣ ግሌን ሄቨን፣ ግሌናላን፣ ኦክላንድ ቴረስ፣ ፓይን ክሬስት፣ ሮክ ቪው፣ ኬምፕ ሚል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች።

**የዳበረ የኤለመንተሪ ትምህርት ማዕከልማለት በ 4ኛ ክፍል የሚጀመር የሁለት ዓመት ፕሮግራም ነው። በቋንቋ ስነጥበብ፣ በሂሳብ፣ በሳይንስ እና በማህበራዊ ጥናቶች ከፍተኛ ተሰጥኦ እና ዝንባሌ ያላቸውን ተማሪዎች ፍላጎቶች ለማሟላት የተዘጋጀ ነው።**

### ወደ ፕሮግራሙ ለመግባት

3ኛ ክፍል ተማሪዎች በሙሉ ለዳበረ የሊተርሲ ትምህርት እና ወደ 4ኛ ክፍል ዝውውር በማእከላዊ ደረጃ ይገመገማሉ። ለማዕከላዊ ግምገማ አካል ጥቅም ላይ የሚውሉ መስፈርቶች የሪፖርት ካርድ ውጤቶች፣ የፈተና ውጤቶች፣ የንባብ ደረጃ እና የተማሪ አገልግሎቶች (IEP፣ ELD፣ 504 ወይም FARMS) ያካትታሉ።

ይህ ሂደት በማዕከላዊ ደረጃ ስለሚካሄደው ግምገማ 3ኛ ክፍል ተማሪዎች ላሏቸው ቤተሰቦች በማሳወቅ ጃኑዋሪ ላይ ይጀመራል። ለበለፀገ/ለዳበረ ፕሮግራም ከተለዩ በኋላ በፕሮግራሙ ውስጥ የሚደረግ ምደባ የሚካሄደው በዕጣ/በሎተሪ ነው። ቤተሰቦች በማዕከላዊ ደረጃ የተደረጉ የግምገማ ውጤቶችን ስፕሪንግ መጀመሪያ ላይ መረጃ ያገኛሉ።

እያንዳንዱ ማእከል በአጠቃላይ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክላስተር በሚሸፍንበት አካባቢ ላይ ትኩረት በመስጠት የተወሰነ ጂኦግራፊያዊ አካባቢን ያገለግላል። ተማሪዎች ወደ ማእከል ለመግባት ብቁ የሚሆኑበት ማእከል የመኖሪያ አድራሻቸው በሚገኝበት ክለስተር ይወሰናል።

### የእርስዎ ተማሪ...

- ልዩ የማመዛዘን ችሎታን መገንባት፣ የላቀ የቃላት አጠቃቀምን፣ የላቀ ደረጃ የጽሑፍ አገላለጽ መገንባትና ማዳበር
- በተለያዩ ሁኔታዎችና አካባቢዎች የመማር፣ የማወቅ ጉጉት፣ እና ውስጣዊ ተነሳሽነት ያሳያል/ታሳያለች?
- ጠንካራ ወሳኝ እና የፈጠራ አስተሳሰብ ያሳያል/ታሳያለች?
- ከፍተኛ ቁርጠኝነት፣ ጽናት እና ነፃነት አላት/አለው?
- በትብብር እና በተናጥል በደንብ ይሰራል/ትሠራለች?
- ስለ ሥነ ጽሑፍ እና ወቅታዊ ሁኔታዎች ውይይት ታደርጋለች/ያደርጋል?

### ለዳበረ ጥናት ወደ አንደኛ ደረጃ ማእከል ያስገቡ።

ፕሮግራሙ የ MCPS ስርአተ ትምህርትን የሚያዳብር፣ የሚያፋጥንና ሠፊ የትምህርት አውድ ይሠጣል። በቋንቋ ስነጥበብ፣ በሳይንስ፣ እና በማህበራዊ ጥናት/ሶሻል ስተዲስ ከፍተኛ ተሰጥኦ ያላቸዉ ተማሪዎችን ፍላጎቶች ለማሟላት የተዘጋጀ ነው። ፕሮግራሙ ከክፍል ደረጃ በላይ የሆኑ ጽሑፎችን ይጠቀማል፣ አጽንኦታዊ አስተሳሰብ፣ እና ችግር መፍታት፣ እና የግንኙነት ችሎታዎችን መገንባት ላይ ያተኩራል።

ለምሳሌ፣ አንድ ተማሪ—

- ርዕስን ወይም ፅንሰ-ሀሳብን ከበርካታ የእውቀት ዘርፍና ትምህርት አንጻር ማጥናት
- ታሪካዊ ክስተቶች ከአሁናዊ ሁነቶች ጋር ያላቸውን ግንኙነቶች መቃኘት/ማጤን
- ለገሃዱ ዓለም ችግሮች መፍትሄዎችን ለመፍጠር በትናንሽ/በአነስተኛ ቡድኖች ተመድበው በትብብር መሥራት

### የፕሮግራም ጥያቄዎች

**የተፋጠነ እና የዳበረ ትምህርት ክፍል**
Division of Accelerated and Enriched Instruction
240-740-3110

### የመግቢያ ጥያቄዎች

**የኮንሶርሽያ ምርጫ እና የማመልከቻ ፕሮግራም አገልግሎት ክፍል**

Division of Consortia Choice and Application Program Services
240-740-7800

www2.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/specialprograms/elementary/center-enriched-studies




MCPS ፕሮግራሞቹ ከሚያገለግሏቸው አካባቢዎች ለተማሪዎች ከአማካይ ቦታዎች ማጓጓዣ ያቀርባል። ስለ "አማካይ ማቆሚያ ቦታዎች" መጓጓዥን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ገጽ 3 ይመልከቱ።

## የአካባቢ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮግራሞች

## የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ዓለም አቀፍ የቋንቋ ኢመርሽን ፕሮግራሞች

## ሂሳብ፣ ሳይንስ፣ የኮምፒተር ሳይንስ ማግኔት ፕሮግራሞች

## ሰብአዊ እና የኮሚዩኒኬሽን ማግኔት ፕሮግራሞች

## የዲጂታል ዲዛይን እና ልማት ማግኔት ት/ቤት

## የማግኔት ትምህርት ቤት የፈጠራ እና የሥነ-ጥበብ አቀራረብ

## የኤሮስፔስ ቴክኖሎጂ ማግኔት ት/ቤት

**ለወላጆች/አሳዳጊዎች እና ተማሪዎች ትኩረት፡ ከዚህ ሕትመት በኋላ አንዳንድ መረጃ ሊለወጥ ይችላል። እባክዎ ይህን በይነመረብ ይጎብኙ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/specialprograms/ ወይም ስለሚገኙት ፕሮግራሞች ይበልጥ ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት ትምህርት ቤቱን ያነጋግሩ።**

# Middle School Application Programs




## Middle School Magnet Consortium (MSMC) Schools

***Argyle Magnet School for Digital Design and Development***
***Loiederman Magnet School for the Creative and Performing Arts***
***Parkland Magnet School for Aerospace Technology***

*Admission is based on a Choice process open to all Montgomery County Grade 5 students in-consortium and out-of-consortium. All Grade 5 students residing in one of the following elementary school service areas must participate in the Choice process: Brookhaven, Georgian Forest, Harmony Hills, Sargent Shriver, Strathmore, Viers Mill, Weller Road, and Wheaton Woods. All other MCPS Grade 5 students are "out of consortia" and may apply to participate in the Choice process.*

## Middle School Immersion Continuation Programs

***Gaithersburg Middle School***
*French and Spanish Immersion Program*
*Students who complete the Maryvale ES French Immersion Program and articulate from Washington Grove ES Two Way Immersion Program may attend automatically. All others interested in participating may contact the school to learn if space is available, and passing a language assessment is contingent upon invitation.*

***Herbert Hoover Middle School***
*Chinese Immersion Program*
*Students who complete the Bayard Rustin ES or Potomac ES Chinese Immersion Program may attend automatically. All others interested in participating may contact the school to learn if space is available, and passing a language assessment is ontingent upon invitation.*

***Lakelands Park Middle School***
*Spanish Immersion Program*
*Students who articulate from Brown Station ES Two Way Immersion Program may attend automatically. All others interested in participating may contact the school to learn if space is available and passing a language assessment is contingent upon invitation.*

***Newport Mill Middle School***
*Spanish Immersion Program*
*Students who articulate from Oakland Terrace ES Two Way Immersion Program may attend automatically. All others interested in participating may contact the school to learn if space is available and passing a language assessment is contingent upon invitation.*

***Odessa Shannon Middle School***
*Spanish Immersion Program*
*Students who articulate from Kemp Mill ES Two Way Immersion Program may attend automatically. All others interested in participating may contact the school to learn if space is available and passing a language assessment is contingent upon invitation.*

***Silver Spring International Middle School***
*French and Spanish Immersion Programs*
*Students who complete the the Sligo Creek ES French or Rolling Terrace ES Two Way Immersion Programs may attend automatically. All others interested in participating may contact the school to learn if space is available, and passing a language assessment is contingent upon invitation.*

***Westland Middle School***
*Spanish Immersion Program*
*Students who complete the Rock Creek Forest ES Spanish Immersion Program may attend automatically. All others interested in participating may contact the school to learn if space is available and passing a language assessment is contingent upon invitation.*

***White Oak Middle School***
*Spanish Immersion Program*
*Students who complete the Burnt Mills or William T. Page ES Spanish Immersion Program may attend automatically. All others interested in participating may contact the school to learn if space is available, and passing a language assessment is contingent upon invitation.*

*See Page 14 for specific information.*

## Middle School Magnet Programs

***Roberto W. Clemente Middle School***
*Mathematics, Science, Computer Science Center Program*
*The following high school clusters will be considered: Clarksburg, Damascus, Gaithersburg, Magruder, Northwest, Poolesville, Quince Orchard, Seneca Valley, Watkins Mill.*

***Eastern Middle School***
*Humanities and Communication Magnet Program*
*The following high school clusters will be considered: Bethesda-Chevy Chase, Blair, Blake, Churchill, Einstein, Kennedy, Walter Johnson, Richard Montgomery, Northwood, Paint Branch, Rockville, Sherwood, Springbrook, Wheaton, Whitman, Wootton.*

***Dr. Martin Luther King Middle School***
*Humanities and Communication Center Program*
*The following high school clusters will be considered: Clarksburg, Damascus, Gaithersburg, Magruder, Northwest, Poolesville, Quince Orchard, Seneca Valley, Watkins Mill.*

***Takoma Park Middle School***
*Mathematics, Science, Computer Science Magnet Program*
*The following high school clusters will be considered: Bethesda-Chevy Chase, Blair, Blake, Churchill, Einstein, Kennedy, Walter Johnson, Richard Montgomery, Northwood, Paint Branch, Rockville, Sherwood, Springbrook, Wheaton, Whitman, Wootton.*

*Montgomery County Public Schools - Division of Capital Planning - July 9, 2025*

## የአካባቢ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮግራሞች

### የሁለተኛ ደረጃ ሥርዓተ ትምህርት ክፍል እና የዲስትሪክት አቀፍ ፕሮግራሞች በሥርዓተ ትምህርት እና ትምህርታዊ ፕሮግራሞች ቢሮ ውስጥ

240-740-3110
www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/enriched/

**የሂሳብ ትምህርት**

240-740-4001
www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/math/

**የቋንቋ ስነጥበብ ትምህርት**

240-740-4006
www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/english/

**የሳይንስ ትምህርት**

240-740-4002
www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/science/

**የማህበራዊ ጥናት ትምህርት**

240-740-4008
www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/socialstudies/

ሁሉም የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎችን ፍላጐት ለማሟላት የተለያዩ የትምህርት መርሀ ግብሮች እና የማበልፀጊያ ፕሮግራሞች አሏቸው፣ ይህም በአንድ በተወሰነ የትምህርት መስክ ከፍተኛ ፍላጎትን፣ ዝንባሌ እና/ወይም የስኬት ደረጃ ለሚያሳዩ ተማሪዎች ጭምር ነው። በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ፣ ሁሉም ተማሪዎች ትምህርታቸዉን የማበልፀግና የማስፋት፣ የሚፈልጉትን መስክ የማጥናትና ማሰስ፣ እናም ተፈታታኝ እና ጥብቅ ስራዎችን ከእኩዮቻቸው ጋር ተባብረው የመሥራት እድል ሊኖራቸው ይገባል። በአካባቢዎ የሚገኝ የመለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስለሚያቀርበው የበለጠ መረጃ ለማግኘት ት/ቤቱን በቀጥታ ያነጋግሩ።

#### የአካባቢዎን ትምህርት ቤት ያነጋግሩ

የአከባቢዎ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስለሚሰጠው ትምህርት የበለጠ ለማወቅ ት/ቤቱን በቀጥታ ያነጋግሩ ወይም MCPS መነሻ ድረገጽ ላይ የትም ህርት ቤቱን ስም በመፈለግ **ይመልከቱ።** ww2.montgomeryschoolsmd.org/schools/

#### በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ፣ ሁሉም ተማሪዎች እድል አላቸው ለ ...

- በየክፍል ደረጃዎቻቸው ያሉትን ማቴሪያሎች በጥልቀት መረዳት እና ማበልጸግ፣
- ከክፍል ደረጃቸውም በላይ የሆኑ ማቴሪያሎችን በጥልቀት የማወቅና የማዳበር,
- የዝንባሌ መስኮችን ማጥናትና ማሰስ፣ እና
- አዳጋችና ጥብቅ በሆኑ ሥራዎች ላይ ከእኩዮች ጋር ተባብሮ መሥራት

#### ከሚሰጡት የበለፀጉ/የዳበሩ ፕሮግራሞች ውስጥ አንዳንድ ምሳሌዎች ...

- የሳይንስ አውደርዕይ
- ኢንተርናሽናል ባካሎሬት የመካከለኛ ዓመት ፕሮግራም
- ዊልያም እና ሜሪ የቋንቋ ስነጥበብ ዩኒት ከፍተኛ የትምህርት ችሎታ ላላቸው ተማሪዎች 6ኛ-8ኛ ክፍል
- የጁንየር ግሬት ቡክስ ፕሮግራም ከ6ኛ-8ኛ ክፍል
- የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሂሳብ ኮርሶች ተደራሽነት
- በፍጥነት የሚካሄዱ እና የዳበሩ/የበለፀጉ ኮርሶች
- የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርሶች ተደራሽነት

# የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዓለም ቋንቋዎች ኢመርዥን ቀጣይ ፕሮግራሞች

## የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዓለም ቋንቋዎች ኢመርሽን ቀጣይ ፕሮግራሞች

የኢመርሽን ፕሮግራሞች በካውንቲው በሚከተሉት ቦታዎች ላይ ይሰጣሉ

ጌትስበርግ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት (Gaithersburg MS)
ፈረንሳይኛ እና ስፓንሽኛ

ኸርበርት ሁቨር መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት (Herbert Hoover MS)
ቻይንኛ

ሌክላንድ ፓርክ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት (Lakeland Park MS)
ስፓኒሽኛ

ኒውፖርት ሚል መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት - Newport Mill MS
ስፓንሽኛ

ኦዴሳ ሻነን መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት (Odessa Shannon MS)
ስፓንሽኛ

ሲልቨር ስፕሪንግ ኢንተርናሽናል መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
ፈረንሳይኛ እና ስፓንሽ/French and Spanish

ዌስትላንድ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስፓንሽ/Spanish

ዋይት ኦክ (White Oak MS) ስፓንሽኛ

## ፈረንሳይኛ እና ስፓኒሽኛ ኢመርዥን ቀጣይ ፕሮግራም

የሜሪቫሌ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት የፈረንሳይኛ "French One-Way Immersion Program" ፕሮግራም ያጠናቀቁ ተማሪዎች ወይም ከጌትስበርግ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ወይም ከዋሽንግተን ግሮቭ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ስፓኒሽኛ "Spanish Two-Way Immersion Program" ኢመርሽን ፕሮግራም የሚመጡ ተማሪዎች በጌትስበርግ መለስተኛ ደረጃ ት/ቤት መከታተል ይችላሉ። ሌሎች ለመሳተፍ የሚፈልጉ ሁሉ ቦታ ካለ ለማወቅ ት/ቤቱን ማነጋገር ይችላሉ፥ ሆኖም የቋንቋ ምዘና ማለፍ የምደባውን ሁኔታ የሚወሰን ይሆናል።

ስላይጎ ክሪክ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ፈረንሳይኛ "One-Way Immersion" ኢመርዥን ወይም ሮሊንግ ቴራስ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ስፓንሽኛ "Two-Way Immersion Programs" ኢመርሽን ፕሮግራሞችን ያጠናቀቁ ተማሪዎች ሲልቨር ስፕሪንግ ኢንተርናሽናል መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት መከታተል ይችላሉ። ሌሎች ለመሳተፍ የሚፈልጉ ሁሉ ቦታ ካለ ለማወቅ ት/ቤቱን ማነጋገር የሚችሉ ሲሆን፣ የቋንቋ ምዘና ማለፍ የምደባውን ሁኔታ ወሳኝ ይሆናል።

በብራውን ስቴሽን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ስፓንሽኛ "Two-Way Immersion Programs" ኢመርሽን ፕሮግራሞችን ያጠናቀቁ ተማሪዎች በአካባቢያቸው መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ሌክላንድስ ፓርክ መከታተል ይችላሉ፣ እና ኬምፕ ሚል አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ስፓንሽኛ "Two-Way Immersion Program" ኢመርሽን ፕሮግራም ያጠናቀቁ ተማሪዎች በአካባቢያቸው ኦዴሳ ሻነን መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መከታተል ይችላሉ፣እና ኦክላንድ ቴራስ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት "Two-Way Immersion Program" ኢመርሽን ፕሮግራም ያጠናቀቁ ተማሪዎች በአካባቢያቸው በኒውፖርት ሚል መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት መከታተል ይችላሉ። ሌሎች ለመሳተፍ የሚፈልጉ ሁሉ ቦታ ካለ ለማወቅ ት/ቤቱን ማነጋገር ይችላሉ፣ ሆኖም የቋንቋ ምዘና ማለፍ ለምደባው ወሳኝ ይሆናል።

## ቻይንኛ ኢመርሽን ቀጣይ ፕሮግራም

ቤያርድ ረስቲን አንደኛ ደረጃ ት/ቤት "One-Way Immersion Program" ኢመርሽን ፕሮግራም ያጠናቀቁ ወይም ከፖቶማክ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ኢመርሽን ፕሮግራም የተውጣጡ ተማሪዎች በቀጥታ በሆቨር መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት መሳተፍ ይችላሉ። ሌሎች ለመሳተፍ የሚፈልጉ ሁሉ ቦታ ካለ ለማወቅ ት/ቤቱን ማነጋገር ይችላሉ፥ ሆኖም የቋንቋ ምዘና ማለፍ የምደባውን ሁኔታ የሚወሰን ይሆናል።

## ዓለም አቀፍ ቋንቋዎች ትምህርት

240-740-4005

www2.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/specialprograms/admissions/immersion

### ወደ ፕሮግራሙ ለመግባት

አለም አቀፍ ቋንቋ ኢመርዥን ፕሮግራሞች መግባት በኤለመንተሪ ት/ቤት ተመሣሣይ የኢመርዥን ፕሮግራም አጠናቀው ወደ 6ኛ ክፍል ለሚመጡ ተማሪዎች ውሱን ነው። በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮግራም ውስጥ ያልተሳተፉ ተማሪዎች በኢመርዥን ፕሮግራሞች ቦታ ከተገኘ ፈተና መውሰድ ይችላሉ። ስለ ማመልከቻ ሂደት እና ስለጊዜ ገደብ ለማወቅ ከፕሮግራሙ የሚመለከታቸውን በቀጥታ ያነጋግሩ።

### የእርስዎ ተማሪ ...ፍላጎት አለው/አላት?

- የሁለተኛ ቋንቋ እውቀታቸውን ማስፋፋት ለመቀጠል?
- በቻይንኛ ማንበብ እና መጻፍ?
- ስለዓለም ክስተቶች በፈረንሳይኛ መወያየት?
- ስለ ስፓንሽ ባህል ጥናት ማድረግ?

ከአንደኛ ደረጃ የፈረንሳይኛ እና የስፓንሽ ኢመርዥን ፕሮግራሞች ለሚመጡ ተማሪዎች፣ የሁለት-ፕሬድ ብሎክ ትምህርት የቋንቋ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ እና የማሕበራዊ ጥናት ኮርሶችን በተመሳሳይ ቋንቋ እንዲያጠናቅቁ ያስችላቸዋል። ከአንደኛ ደረጃ የቻይንኛ ኢመርዥን ፕሮግራሞች የሚመጡ ተማሪዎች ወደ MCPS 7ኛ ክፍል መደበኛ ቻይንኛ 2 ኮርስ ከመሻገራቸው አስቀድሞ በአንድ ክፍለ-ጊዜ የቋንቋ ኮርስ ምድብ ይቀጥላሉ።

### ከመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች የአለም ቋንቋዎች ኢመርዥን ቀጣይ ፕሮግራሞች በአንዱ ኢመርዥን ፕሮግራም የመቀጠል ዝንባሌ።

- ፖቶማክ እና ባያርድ ረስቲን አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሁቨር መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
- ሜሪቫሌ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ዋሽንግተን ግሮቭ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ጌትስበርግ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጌትስበርግ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
- ዊልያም ቲ. ፔጅ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በርንት ሚልስ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋይት ኦክ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
- ስላይጎ ክሪክ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እናሮሊንግ ቴራስ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲልቨር ስፕሪንግ ኢንተርናሽናል መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
- የሮክ ክሪክ ፎረስት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዌስትላንድ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
- ብራውን ስቴሽን አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሌክላንድስ ፓርክ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
- ኬምፕ ሚል አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኦዴሳ ሻነን መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት
- ኦክላንድ ቴሬስ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኒውፖርት ሚል መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት

የእያንዳንዱን ትምህርት ቤት ድረ ገጽ ለመጎብኘት፣ የትምህርት ቤቱን ስም MCPS በይነመረብ መነሻ ገጽ ላይ ይፈልጉ ወይም www.montgomeryschoolsmd.org/schools/ ይጎብኙ።




2025–26 SY የትምህርት አመት፣ ለጌትስበርግ፣ ሲልቨርስፕሪንግ ኢንተርናሽናል፣ ዌስትላንድ እና ዋይት ኦክ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስን ማዕከላዊ የመጓጓዣ ማቆሚያ ቦታ ይኖራል። ስለ ማእከላዊ የማቆሚያ ቦታ መጓጓዣ ዝርዝር ለማግኘት ገጽ 3 ላይ ይመልከቱ። ሌሎች ፕሮግራሞች በሙሉ የአካባቢ መጓጓዣ ብቻ ያገኛሉ።

# ሂሳብ/ሳይንስ/ኮምፒውተር ሳይንስ ማግኔት ፕሮግራም

## ሮቤርቶ W. ክለመንቴ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት

Roberto W. Clemente Middle School
18808 Waring Station Road
Germantown, MD 20874
301-284-4744

## ታኮማ ፓርክ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት

Takoma Park Middle School (TPMS)
7611 Piney Branch Road
Silver Spring, MD 20910
240-740-5220

የሂሳብ / ሳይንስ / ኮምፒተር ሳይንስ ማግኔት ፕሮግራም በሦስት የትኩረት ዘርፎች ማለትም ሂሳብ፣ ሳይንስ እና ኮምፒተር ሳይንስ ልዩ ችሎታን የሚፈትን የትምህርት እድሎችን ይሰጣል። ተማሪዎች በፕሮብሌም-አፈታት ዘዴ በመጠቀም የትምህርት ይዘቶችን እንዲያገናኙ ይደፋፈራሉ። ተማሪዎች ለምሳሌ፡- ከሳይንቲስቶች ጋር እና ከሂሳብ ሊቃውንት ጋር አብሮ መሥራት፣ በአካደሚ ውድድሮች መሣተፍ፣ እና የኮምፒውተር ፕሮግራሞችን መጻፍ የመሣሠሉ የተለያየ ዓይነት በርካታ ልዩ አካደሚክ ልምምዶችን ያገኛሉ። የወላጅ/አሳዳጊ መረጃ በልዩ ፕሮግራሞች ድረ ገጽ ላይ ቪዲዮ ይለጠፋል፣ www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/specialprograms/middle/. የዝግጅት አቀራረቡ ስለ ፕሮግራሙ እና ስለ አቀባበል ሂደት ዝርዝር ያስረዳል። በካውንቲው በሙሉ ከሚገኙ ማዕከላዊ ቦታዎች ወደ እያንዳንዱ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የደርሶ መልስ የአውቶቡስ አገልግሎት ይሰጣል።

### ወደ ፕሮግራሙ ለመግባባት

ሁሉም የ5ኛ ክፍል ተማሪዎች በአካባቢያቸው ትምህርት ቤት ወይም ማግኔት ፕሮግራም ለመለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዳበረ እና ፈጣን ትምህርት ፕሮግራም የማዕከላዊ ግምገማ አካል ይሆናሉ። በማዕከላዊ ግምገማ ተለይተው በሎተሪ ዝርዝር ውስጥ ይቀመጣሉ፥ ከዚያም በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የበለፀጉ ትምህርቶችን የመከታተል እድል ይሰጣቸዋል። ለሪጅን መቀመጫ ሎተሪ ዕጣ ይካሄዳል በማዕከላዊ ግምገማ አካል ጥቅም ላይ የሚውሉ መስፈርቶች የሪፖርት ካርድ ውጤቶች፣ የፈተና ውጤቶች፣ የንባብ ደረጃ እና የተማሪ አገልግሎቶች (IEP፣ ELD፣ 504 ወይም FARMS) ይካተታሉ። ምንም የወላጅ/አሳዳጊ ማመልከቻ አይኖርም።

ይህ ሂደት ኦክቶበር ላይ Virtual Regional Magnet Presentation ይጀመራል፤ እና 5ኛ ክፍል ተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች በማዕከላዊ ደረጃ የተካሄደው የግምገማ እና የዕጣ/ሎተሪ ውጤቶችን በተመለከተ ጃንወሪ ወር ላይ መረጃ ያገኛሉ።

እርስዎ በሚኖሩበት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክላስተር እያንዳንዱ ማዕከል የተወሰነ ጂኦግራፊያዊ አካባቢ ያገለግላል።

### የእርስዎ ተማሪ ...አለው/አላት?

- በሂሳብ ከፍተኛ ፍላጎት እና ችሎታ
- ኮምፒውተሮች እንዴት እንደሚሰሩ እና ስለ አፕሊኬሽኖቻቸው ጥልቅ ግንዛቤን ለማዳበር ጠንካራ ተነሳሽነት?
- በሳይንስ ወቅታዊ ሁነቶች እና ሳይንሳዊ ጥናት/ምርምር የማካሄድ ጥልቅ ፍላጎት?
- አዎንታዊ አመለካከት እና ከእኩዮች ጋር በትብብር ለመስራት ቁርጠኝነት?

### በታኮማ ፓርክ መለስተኛ ደረጃ ት/ቤት ወይም ሮቤርቶ W. ክሌሜንቴ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የሂሳብ፣ ሳይንስ፣ ኮምፒውተር ሳይንስ ማግኔት ፕሮግራም ላይ ለመሳተፍ አስቡበት።

ከፈጣን የሂሳብ ትምህርት፣ ሳይንስ፣ እና የኮምፒዩተር ኮርሶች በተጨማሪ ተማሪዎች ከመንግስት ድርጅቶች፣ ከአካባቢ ዩኒቨርሲቲዎች እና ድርጅቶች ጋር የሳይንስና ሂሳብ አዋቂዎች ጋር ሊሰሩ ይችላሉ። ፕሮግራሙ እንደ "Continental Math League—Math and computer divisions፡ Montgomery County Area Science Fair፡ and American Computer Science League" የመሳሰሉ በርካታ የአካዳሚክ ውድድሮች ተደራሽነት ይኖረዋል። በተጨማሪም ተማሪዎች "area creeks እና Smithsonian's Naturalist Center" ማእከል ሳይንሳዊ የመስክ ሥራዎችን ያካሂዳሉ። በሁሉም ልዩ የትምህርት/የኮርስ ስራዎቻቸው፣ ተማሪዎች በሂሳብ፣ በኮምፒዩተር ሳይንስ፣ እና በሳይንሳዊ አሠራር የተጨባጨን ዓለም ችግሮች ለመፍታት እራሳቸውን ችለው ለመመራመር በአንድ የአካዳሚክ ቡድን/ጓድ ጋር ይሰራሉ።

MCPS በሮቤርቶ W. ክሌመንት መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት እና ታኮማ ፓርክ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ማግኔት ፕሮግራሞች ከሚያገለግሉባቸው ቦታዎች ላሉ ተማሪዎች ከአማካይ የአውቶቡስ መቆሚያ መጓጓዣ ይሰጣል። ስለ "ማዕከላዊ የትራንስፖርት ማቆሚያዎች" መጓጓዥን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ገጽ 3 ይመልከቱ።

## ሰብአዊነት እና ኮሙዩኒኬሽን ማግኔት ፕሮግራም

### ኢስተርን መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት
### Eastern Middle School

300 University Blvd., East
Silver Spring, MD 20901
240-740-6305

Eastern Humanities and Communication Program

### ዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁር. መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት

13737 Wisteria Drive
Germantown, MD 20874
240-740-6350

የስነ-ሰው እና የተግባቦት/ኮሙኒኬሽን ማግኔት ፕሮግራሞች ልዩ እና ችሎታን የሚፈታተን የትምህርት እድሎችን በሶስት ዘርፎች ይሰጣል፥- ስነ-ጽሑፍ፣ ሚዲያ ፕሮዳክሽን፣ እና የዓለም ጥናቶች። ተማሪዎች በሃሳቦች መካከል ያሉትን ግንኙነቶች እንዲያያይዙ፣ በተመረጡ ርእሶች በጥልቀት ጥናት እንዲያደርጉ፣ እና የፈጠራ አስተሳሰብ ችሎታን እንዲያዳብሩ ይበረታታሉ። ማግኔት ፕሮግራም ውስጥ ያሉ ተማሪዎች እንግሊዝኛን፣ ሚዲያ ፕሮዳክሽን፣ እና ወርልድ ስተዲስ 3 የማግኔት ኮርሶችን ይወስዳሉ። ከማግኔት ፕሮግራም ውጪ ያሉ ተማሪዎች ሳይንስ፣ ሂሳብ፣ የአካል ማጎልመሻ ትምህርትን ጨምሮ ሰፋፊ ኮርሶችን ይወስዳሉ፤ እና ወርልድ ላንጉጅ ለመውሰድ መመዝገብ ይችላሉ። የወላጅ/አሳዳጊ መረጃ በልዩ ፕሮግራሞች ድረ ገጽ ላይ ቪዲዮ ይለጠፋል፣ www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/specialprograms/middle/. የዝግጅት አቀራረቡ ስለ ፕሮግራሙ እና ስለ አቀባበል ሂደት ዝርዝር ያስረዳል። በካውንቲው በሙሉ ከሚገኙ ማዕከላዊ ቦታዎች ወደ እያንዳንዱ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የደርሶ መልስ የአውቶቡስ አገልግሎት ይሰጣል።

### ወደ ፕሮግራሙ ለመግባት

ሁሉም የ 5ኛ ክፍል ተማሪዎች በአካባቢያቸው ትምህርት ቤት ወይም ማግኔት ፕሮግራም ለመለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዳበረ እና ፈጣን ትምህርት ፕሮግራም የማዕከላዊ ግምገማ አካል ይሆናሉ። በማዕከላዊ ግምገማ ተለይተው በሎተሪ ዝርዝር ውስጥ ይቀመጣሉ፥ ከዚያም በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የበለፀጉ ትምህርቶችን የመከታተል እድል ይሰጣቸዋል። ለሪጅን መቀመጫ ሎተሪ ዕጣ ይካሄዳል ለማዕከላዊ ግምገማ አካል ጥቅም ላይ የሚውሉ መስፈርቶች የሪፖርት ካርድ ውጤቶች፣ የፈተና ውጤቶች፣ የንባብ ደረጃ እና የተማሪ አገልግሎቶች (IEP፣ ELD፣ 504 ወይም FARMS) ያካትታሉ። ምንም የወላጅ/አሳዳጊ ማመልከቻ አይኖርም።

ይህ ሂደት ኦክቶበር ላይ Virtual Regional Magnet Presentation ይጀመራል፤ እና 5ኛ ክፍል ተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች በማዕከላዊ ደረጃ የተካሄደው የግምገማ እና የዕጣ/ሎተሪ ውጤቶችን በተመለከተ ጃንወሪ ወር ላይ መረጃ ያገኛሉ።

እርስዎ በሚኖሩበት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክላስተር እያንዳንዱ ማዕከል የተወሰነ ጂኦግራፊያዊ አካባቢ ያገለግላል።

### የእርስዎ ተማሪ ...ዝንባሌ አለው/አላት ወይ?

- የስነ-ጽሑፍ ከፍተኛ ፍላጎት እና ችሎታ?
- በስነ-ሰው ወይም በመገናኛ ብዙሃን ስነጥበባዊ ፕሮዳክሽን ላይ ጠንካራ ተነሳሽነት?
- በታሪክ፣ ጂኦግራፊ፣ ኢኮኖሚክስ እና ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ጥልቅ ፍላጎት?
- አዎንታዊ አመለካከት እና ከእኩዮች ጋር በትብብር ለመስራት ቁርጠኝነት?

### በዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይም በኢስተርን መለስተኛ ደረጃ ት/ቤት የስብእና እና የኮሙኒኬሽን ፕሮግራም ላይ ለመሳተፍ አስቡበት።

ተማሪዎች በስነ-ጽሑፍ ጠንካራ የኮርስ ሥራዎችን የመሥራት እና በቴሌቪዥን፣ ሬድዮ እና ፊልም ሕትመትና ሥርጭት እድሎች ይኖራቸዋል። ተማሪዎች የአቋም መግለጫዎችን፣ ድራማዎች፣ በራሪ ጽሑፎች፣ የመጽሔት አምዶችን እና የምርምር ወረቀቶችን በፈጠራ ያዘጋጃሉ። እንዲሁም በፕሮግራሙ የቴሌቪዥን ስቱዲዮዎች ውስጥ በፕሮዳክሽን ቡድን አባልነት በተግባር ሥራ የመሣተፍ/የመሥራት እድሎችን ያገኛሉ። ተማሪዎች እንደ ትርኢት አቅራቢዎች፣ ሲኒማቶግራፊርነት፣ በአዘጋጅነት፣ እንደ ዳይሬክተርነት፣ የኦዲዮ መሐንዲስነት፣ አርታዒያን እና የግራፊክ አርቲስቶች በመሆን በቡድን ይሰራሉ። ተማሪዎች ታሪካዊ ክስተቶችን፣ ስነ-ጽሁፍን እና ስነ-ጥበብን በመተንተን የሰውን ተሞክሮ ያጠናሉ። በተጨማሪም የሰውን ተሞክሮ በፅሁፍ እና በምስል/በሚታዩ ሚዲያዎች አማካይነት መዘገብን/መሰነድን ይማራሉ።

MCPS በዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁንየር መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት እና ኢስተርን መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ማግኔት ፕሮግራሞች ለሚማሩ ተማሪዎች ከማዕከላዊ የአውቶቡስ ማቆሚያ ሥፍራዎች በመነሣት ፕሮግራሙ ለሚያገለግላቸው አካባቢዎች የትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣል። ስለ "ማዕከላዊ የአውቶቡስ ማቆሚያዎች" መጓጓዣን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ገጽ 3 ይመልከቱ።

# ዲጅታል የንድፍ ሥራ እና ዴቨሎፕመንት
# Digital Design and Development

## አርጌይል መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት
## Argyle Middle School

2400 Bel Pre Road
Silver Spring, MD 20906
240-740-6370
www.montgomeryschoolsmd.org/schools/msmagnet/argyle/

ዲጂታል ዲዛይን እና ግንባታ በ 6ኛ፣ 7ኛ፣ እና 8ኛ ክፍል ለሚገኙት ተማሪዎች በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ልማትና አተገባበር ላይ ያተኮረ ችሎታን ፈታኝ የሆነ የትምህርት ፕሮግራም ያቀርባል። ተማሪዎች የት/ቤት አሠራር ልምድን ለማሻሻል የቴክኖሎጂ መሳሪያዎችን መጠቀም ይማራሉ። ተማሪዎች በዓመት ቢያንስ አንድ የቴክኖሎጂ ኮርስ መውሰድ ይጠበቅባቸዋል። በተጨማሪም፣ተማሪዎች በፕሮግራሚንግ፣ በሳይበር ደህንነት፣ በኤንጂኒሪንግ/በምህንድስና፣ በዲጂታል ዲዛይን እና በዲጂታል ሚዲያዎች ላይ የሚያተኩሩ ተመርጠው የሚወሰዱ/ኢሌክቲቭ የቴክኖሎጂ ኮርሶችን የመውሰድ አማራጭ ይኖራቸዋል። የኮርስ ሥራን ለመደገፍ የቡድን ሥራ እና ፉክክርን መጠቀም፣ የትምህርት ቤት አካባቢ ድባብ ጠንካራ የትብብሮሽ አውድ ነዉ። በጠቅላላው የአርጊየል (Argyl) ልምድ፣ ተማሪዎች በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ስኬታማ የሚሆኑበትን እውቀት እንዲያገኙ እና ወደ ሥራ ለማሸጋገር የሚችሉ ክህሎቶችን ያዳብራሉ።

### ወደ ፕሮግራሙ ለመግባት

ለዲጂታል ዲዛይን እና እድገት ለአርጊየል መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት (Argyle Middle School) መመዝገቢያው በእጣ ላይ የተመሰረተ ነው። በአርገይል (Argyle)፣ በሎይደርማን (Loiederman)፣ እና በፓርክላንድ (Parkland) ኮንሰርትየም የመማሪያ ክልል ውስጥ የሚኖሩ ተማሪዎች 5ኛ ክፍል በምርጫ ሂደት ውስጥ መሳተፍ አለባቸው። ከኮንሰርቲየም አካባቢ ውጭ ለሚገኙ የ5ኛ ክፍል ተማሪዎች በኦንላይን የምርጫ ቅጾች፡- www2.montgomeryschoolsmd.org/school-info/msmagnet/ ወይም የኮንሰርቲያ ምርጫ እና የማመልከት ፕሮግራም አገልግሎቶች ክፍል 240-740-7800።

### የእርስዎ ተማሪ ... ይወዳል/ትወዳለች ወይ?

- በከፍተኛ/ጠንካራ የሒሳብ ችሎታን ተፈታታኝ ኮርሶች?
- ኮምፒውተሮች፣ የቪዲዮ ጨዋታዎች፣ አኒሜሽን፣ 3D እና ግራፊክ ዲዛይን፣ ፕሮግራሚንግ፣ ቪዲዮ ፕሮዳክሽን?
- ዲጂታል መሳሪያዎችን በመጠቀም አዳዲስ መረጃ/ኢንፎርሜሽን መማር እና ፕሮብሌም መፍታት?
- የኮምፒተር ፕሮግራሞችን እና ዲጂታል ስነጥበብን መፍጠር?
- በርካታ የሚዲያ አቀራረቦችን ማዘጋጀት?
- ሐሳቦችን ለመግለፅ የቴክኖሎጂ መሳሪያዎችን መጠቀም?

### ለአርገይል መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ማመልከትን ግንዛቤ ዉስጥ ያስገቡ።

